# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሠ/መ/ቁጥር 220553

ጥቅምት 28 ቀን 2015 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች፡- ኢንተርናሽናል ትሬዲንግ ማኑፋክቸርንግ ሰርቪስ አ.ማ

ተጠሪ፡- አቶ ኑረዲን መሀመድ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በዕቃዉ ጉድለት ምክንያት የሽያጭ ዉል ለማስፈረስ ገዥ ያለበትን ግዴታ የሚመለከት ነዉ፡፡ተጠሪ በሐረሪ ክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ በመሰረቱት ክስ አመልካች ከሚያስመጣቸዉ ኪነቲክ ዊንግ(kinetic wing) የሚባል ባጃጅ ተሽከርካሪዎች መካከል በቀን 15/07/2007ዓ/ም በተደረገ የሽያጭ ዉል አመልካች ለተጠሪ በብር 69,999.99 አንድ ተሽከርካሪ ሽጧል፡፡አመልካች የተሽከርካሪዉን የባትሪ ክፍል በባለሙያ እንደሚያስተካክል ለተጠሪ ቃል ገብቷል፡፡ሆኖም በገባዉ ቃል መሰረት አልፈጸመም፡፡ከአመልካች ሌላ ይህንን ተሽከርካሪ የሚያስመጣ ባለመኖሩ ተጠሪ ለማስጠገን አልቻለም፡፡በዚህ ምክንያት ተጠሪ በተሽከርካሪዉ መገልገል አልቻልኩም፡፡ ስለሆነም አመልካች በዉሉ መሰረት አስተካክሉ እንዲፈጽም አሲያም ዉሉ ሙሉ በሙሉ ቀሪ እንዲሆን እንዲወሰንልኝ፡፡እንዲሁም ተሽከርካሪዉን አገልግሎት ላይ ማዋል ባለመቻሉ በቀን ብር 200.00 ለሁለት ዓመት ከ3

ወር ገቢ አሳጥቶኛል።ተሽከርካሪዉን ለማሰራት ብር 3700.00 ወጪ አስጥቻለሁ። ስለሆነም አመልካች በድምሩ ብር 285,700.00 እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል።

አመልካች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማስቀደም በሰጠዉ መልስ የአመልካች ክስ የማቅረብ መብት በይርጋ ቀሪ የሆነ ነዉ።አመልካች ተሽርካሪዉን ከህንድ አገር ያስመጣዉ በአዲስነቱ ነዉ።ተሽከርካሪዉ ችግር ካለበትና ያለመስተካከሉን ከተረዱ በወር ዉስጥ ተጠሪ ማሳወቅ ነበረባቸዉ።ተጠሪ ተሽከርካሪዉን ከገዙ ከ3 ዓመት በኋላ ያቀረበዉ ክስ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2298/1 እና 2299/1 ስር የተደነገገዉን እና በሰ/መ/ቁጥር 55229 ላይ የተሰጠዉን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሚቃረን ነዉ።ተጠሪ ግዥ ከመፈጸማቸዉ በፊት 3 ቀን ቀድመዉ ተሽከርካሪዉን በራሳቸዉ ባለሙያ በማስነዳት ችግር እንደሌለበት አረጋግጠዋል።በዚሁ መሰረት ግዥ ፈጽመዋል።ተሽከርካሪዉን ከተረከቡ በኋላ ለ3 ወር ያለምንም ችግር አሽከርክረዉ አይተዋል።ችግሩ ሲከሰት የቻለዉ ተጠሪ የተሽከርካሪዉን ባትሪ ለረጅም ጊዜ ሳይነቅሉ በማቆማቸዉ ምክንያት እንጂ ተሽከርካሪዉ ለዚህ የሚያበቃ ችግር ኖሮበት አይደለም።ስለሆነም በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2293/2፣2296 እና 2330 ስር በተደነገገዉ መሰረት ዉሉን የሚያስፈርስ እና አመልካች የሚጠየቅበት ምክንያት የለም።የባትሪ ችግር ቢኖር እንኳን ባትሪዉን ማስቀየር እየተቻሉ በባትሪ ምክንያት ተሽከርካሪዉ ለረጅም ጊዜ ቆሟል በማለት ተጠሪ የተቋረጠ ገቢ በሚል አስልተዉ ሊጠይቁ አይችሉም።ተጠሪ ተሽከርካሪዉ የባትሪ ጉድለት ችግር እንዳለበት ለአመልካች ሳያሳዉቁ በትንሽ ወጪና በቀላሉ የሚስተካከል ነገር ከ3 ዓመት በላይ አቆይተዉ አመልካች እንዲያስተካክል፣ዉሉ እንዲፈርስና ኪሳራ እንዲከፈላቸዉ ያቀረቡት ክስ የሕግ ድጋፍ የለዉም በማለት ተከራክሯል።

ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 17126 ላይ ግራ ቀኝን አከራክሮ በሰጠዉ ዉሳኔ ተጠሪ ክሱን ሳያቀርቡ የቆዩት አንገታቸዉ የአመልካች የቦርድ አባል በመሆናቸዉ ለአገታቸዉ ባላቸዉ ከበሬታ በመነጨ ስሜትና በመካከላቸዉ ባለዉ ዝምድና ትስስር ምክንያት ነዉ በሚል ተጠሪ ያቀረቡትን መከራከሪያ በመቀበል የይርጋ ጊዜ አቆጣጠር በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1853/1 መሰረት ተቋርጧል ሲል አመልካች ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በሚል ያቀረበዉን መቃወሚያ ዉድቅ ማድረጉን ከይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት ዉሳኔ ላይ ተረድተናል።ዋናዉን ጉዳይ በተመለከተ ደግሞ በቀን 13/05/2012ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ ተጠሪ ከአመልካች የገዙት ተሽከርካሪ አዲስ መሆኑን ግራ ቀኝ አልተካካዱም።ተጠሪ ግዥ ሲፈጽሙ ራሳቸዉ በሚያምኑት ባለሙያ ተሽከርካሪዉን አስፈትሸዉና ነድተዉ ካዩ በኋላ መግዛታቸዉን አልካዱም። በምስክሮችም ይሄዉ ተረጋግጧል። ተጠሪ የተሽከርካሪዉን ዋጋ የከፈሉትም ተሽከርካሪዉን ለሳምንት ያህል አሽከርክረዉ ካዩ በኋላ እንደሆነ በምስክሮች ተመስክሯል። በዚህ መሰረት አመልካች ለተጠሪ የሸጠዉ እና ያስረከበዉ ተሽከርካሪ ጉድለት የሌለበት መሆኑ ተረጋግጧል። ተጠሪ ተሽከርካሪዉ ላይ ጉድለት ሲያገኙ በ3 ወር ጊዜ ዉስጥ ለአመልካች ማሳወቅ ነበረባቸዉ። አመልካች ለዚህ ጊዜ ዋቢ የሆነ ቢሆንም ለ3 ዓመታት በግቢዉ ዉስጥ አቁመዉ አቆይተዉ ያቀረቡት ክስ መሆኑን የአመልካች ምስክሮች አስረድተዋል።በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2293 መሰረት ተጠሪ ጉድለቱን ወዲያዉ ማሳወቅ ሲገባቸዉ አላሳወቁም።አሳዉቀዋል ቢባል እንኳን ያሳወቁት ከ2 ዓመት በኋላ ነዉ። ተጠሪ በራሳቸዉ በፈጠሩት ከፍተኛ

ችልተኝነት ምክንያት ተሽከርካሪዉ ለረጅም ጊዜ ቆሞ በመቆቱ የደረሰ ጉዳት ከሚባል በስተቀር አመልካች ጉድለት ያለበትን ተሽከርካሪ አስረክቧል የሚያስብል በቂ ማስረጃ አልተገኘም፡፡በመሆኑም ዉሉ ሲፈርስ እና አመልካች የሸያጩን ዋጋ ሲመልስ አይገባም፡፡ እንዲሁም ተጠሪ በፈጠሩት ቸልተኝነት እና በአጭር ጊዜ ተሽከርካሪዉን ለማስጠገን በቅን ልቦና ባለመንቀሳቀሳቸዉ የተቋረጠ ገቢ በመሆኑ አመልካች ኪሳራ ሊከፍል አይገባም በማለት ክሱን ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡

ተጠሪ በዉሳኔዉ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 05072 ላይ አቅርበዉ ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 13/11/2013ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ የተጠሪ ምስክሮች እና 1ኛ የአመልካች ምስክር በሰጡት ቃል የተሸጠዉ ተሽከርካሪ ጉድለት ያለበት መሆኑን ፍርድ ቤቱ ተረድቷል፡፡ተጠሪ በቀን 15/06/2009ዓ/ም የሰጡት ማስጠንቀቂያም ይህንኑ ያሳያል፡፡ ኪነቲክ ዊንግ(kinetic wing) የሚባል ባጃጅ ተሽከርካሪዎች በከተማይቱ ታርጋ ለጥፈዉ የታክሲ አገልግሎት ሲሰጡ የማይታዩ መሆኑ አገር የሚያዉቀዉ ጸሐይ የሞቀዉ(Judicial Notice) ነዉ፡፡በግራ ቀኙ ምስክሮችም ተረጋግጧል፡፡ ተሽከርካሪዎቹ ለታክሲ አገልግሎት ጥቅም ላይ ያልዋሉ መሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2289 መሰረት ተሽከርካሪዎቹ ጉድለት እንዳለባቸዉ ያስረዳል፡፡ ተጠሪ ተሽከርካሪዉ ለታክሲ አገልግሎት እንደማይዉል ቢያዉቁ ኖሮ ግዡ የማይፈጸሙ መሆኑን ፍርድ ቤቱ ተረድቷል፡፡ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት በግራ ቀኙ መካከል የተደረገ የሽያጭ ዉል ጉድለት የሌለበት ነዉ ሲል የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2289፣2287፣2293/3፣2295/2 — 2297 ስር የተደነገገዉን እና በሰ/መ/ቁጥር 133398 ላይ የተሰጠዉን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሚቃረን ነዉ፡፡በመሆኑም ዉሉ ጉድለት ያለበት ስለሆነ ፈርሶ ግራ ቀኙ ወደነበሩበት ሲመለሱ ይገባል በማለት አመልካች ለተጠሪ ብር 66,999.99 እንዲከፍል ወስኗል፡፡በመቀጠል አመልካች አቤቱታዉን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም ችሎቱ በመ/ቁጥር 00230 ላይ በቀን 07/03/2014ዓ/ም በሰጠዉ ትእዛዝ አቤቱታዉን ሰርዞበታል፡፡

አመልካች በቀን 30/05/2014 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበዉ ከላይ በተገለጸዉ መሰረት በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታዉ ይዘት በአጭሩ፡- የስር ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረበዉን የይርጋ መቃወሚያ ተጠሪ የአመልካች የቦርድ አባል በመሆኑ ባለኝ የቅርብ ዝምድና ምክንያት ክሱን ሳያቀርቡ እንደቆዩ የገለጹትን ምክንያት በመቀበል መቃወሚያዉን ዉድቅ በማድረግ የሰጠዉ ዉሳኔ በሰ/መ/ቁጥር 55229 ላይ የተሰጠዉን የሕግ ትርጉም እና በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2298/1 እና 2299/1 ስር የተደነገገዉን የሚቃረን ነዉ፡፡ተጠሪ በቀን 15/06/2009ዓ/ም ጻፍኩኝ ያሉት ማስጠንቀቂያ ለአመልካች አልደረሰኝም፡፡ ማስጠንቀቂያዉ የደረሰኝ ስለመሆኑ ማረጋገጫ የሚሆን ማስረጃ ተጠሪ አላቀረቡም፡፡ በተሽከርካሪዉ ላይ ጉድለት የተከሰተዉ ተሽከርካሪዉ ለረጅም ጊዜ በተጠሪ ግቢ ዉስጥ በመቆሙ ምክንያት መሆኑን በማስረጃ አስረድተናል፡፡ይህም የሚያሳየዉ ጉድለቱ በአመልካች ጥፋት የተከሰተ አለመሆኑን ወይም በማጭበርበር የደበቀዉ ጉድለት አለመሆኑን ነዉ፡፡በተሽከርካሪዉ ላይ የተከሰተዉ ጉድለት የባትሪ ሆኖ እያለ ዉሉን ለማፍረስ የሚያበቃ መሰረታዊ ጉድለት ሳይኖር ዉሉ እንዲፈርስ የተሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2287 እና 2288/ሀ ስር

*ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

የተደነገገዉን እንዲሁም በሰ/መ/ቁጥር 24974 እና 138386 ሳይ የተሰጠዉን የሕግ ትርጉም የሚቃረን ነዉ፡፡ተሽከርካሪዉን ተጠሪ ራሱ በአመነዉ ባለሙያ አስፈትሾ ጉድለት የሌለበት መሆኑን አረጋግጦ ግዥ መፈጸሙ እና የባትሪ ችግር የተከሰተዉ በአመልካች ጉድለት ምክንያት መሆኑ ባልተረጋገጠበት ዉሉን ተጠሪ አይዋዋልም ነበር በሚል በስር ፍርድ ቤት በግምት ሳይ ተመስርቶ ዉሉ እንዲፈርስ መወሰኑ ስህተት ነዉ፡፡ አመልካች እነዚህን ተሽከርካሪዎች ከሕንድ አገር ሲያስመጣ የነበረዉ በዋናነት ለአዳማ ከተማ ሲሆን በሀረሪ ከተማ በቁጥር ከ10 የማይበልጡ ሲሆኑ የመጨረሻዉን ተጠሪ ገዝተዋል፡፡አመልካች ማስመጣት ያቆመዉ አምራቹ ተሽከርካሪዉን ማምረት ስለተወ እንጂ ተሽከርካሪዉ በባለሙያ ተረጋግጦ ችግር አለበት በመባሉ አይደለም፡፡ስለሆነም ዉሉን የሚያስፈርስ መሰረታዊ የዉል መጣስ ሳይከሰት ዉሉ እንዲፈርስ የተሰጠዉ ዉሳኔ በሰ/መ/ቁጥር 133398 ሳይ የተሰጠዉን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሚቃረን መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በማለት አቤቱታዉን አቅርቧል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ተሽከርካሪ በባለሙያ አስፈትሸዉ ግዥ በመፈጸም ተረክበዉ ከሁለት ዓመት በላይ ሲገለገሉበት የቆዩ ስለመሆኑ በተገለጸበት፣ ተሽከርካሪዉ የባትሪ ችግር ያለበት ስለመሆኑ በአጭር ጊዜ ዉስጥ ለአመልካች ሳያሳዉቁና የተፈጠረዉ ችግር መሰረታዊ የዉል መጣስ ያስከተለ ስለመሆኑ ባላስረዱበት የደርጋ መቃወሚያ ዉድቅ ተደርጎ ዉሉ ፈራሽ እንዲሆን እና ተከራካሪ ወገኖች ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ የተወሰነበትን አግባብነት ከፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2292/1፣2298/1 እና ተከታይ ድንጋጌዎች እንዲሁም በሰ/መ/ቁጥር 552229 ሳይ ከተሰጠዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም አንጻር ተጠሪ ባሉበት እንዲመረመር ትእዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ በቀን 02/09/2014ዓ/ም የተጻፈ መልስ አቅርበዋል፡፡

በሰበር አጣሪ ችሎት በተያዘዉ ጭብጥ ሳይ በተገለጸዉ መሰረት ተጠሪ ተሽከርካሪዉን ከ2 ዓመት በላይ አልተገለገልኩም፡፡ተሽከርካሪዉ ሲሽከረከር ባለመቻሉ ለምርመራ መንገድ ትራንስፖርት መዉሰድ ባለመቻሉ ገና ለተሽከርካሪዉ ሰሌዳ አልወጣለትም፡፡የደርጋ ጊዜ ተቋርጧል በሚል የደርጋ መቃወሚያዉ ዉድቅ መደረጉ በአግባቡ ነዉ፡፡ማስጠንቀቂያ ከሰጠሁበት ቀን ጀምሮ ሲቆጠር ክስ የማቅረብ መብቴ በደርጋ አልታገደም፡፡ ተሽከርካሪዉ ያለበት ጉድለት ለትንራንስፖርት አገልግሎት እንዳይዉል የሚያደርግ አይነተኛ ጉድለት ነዉ፡፡ዉሉን በተዋዋልኩበት ጊዜ ይህ ጉድለት እንዳለበት ባዉቅ ኖሮ በፍጹም የሽያጭ ዉሉን አልፈጸምም ነበር፡፡ይህም በይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት ተረጋግጦ የተወሰነ ነዉ፡፡ስለሆነም ዉሉ እንዲፈርስ የተሰጠዉ ዉሳኔ በሰ/መ/ቁጥር 133398 እና 138386 ሳይ የተሰጠዉን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት ያደረገ ነዉ በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም በቀን 22/09/2014ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርባል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለመልኩ የተመለከተዉ የግራ ቀኙ ክርክርና በየደረጃዉ ባሉ የክልል ፍርድ ቤቶች  የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም ሰበር አጣሪ ችሎት የያዘዉን ጭብጥ ከግምት በማስገባት አመልካች ያቀረበዉ የደርጋ መቃወሚያ ዉድቅ ተደርጎ በመወሰኑ እና የተሽከርካሪ ሽያጭ ዉል ፈርሶ ግራ ቀኙ ወደነበሩበት

እንዲመለሱ በመወሰኑ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል።

እንደመረመርነዉም ተጠሪ በአመልካች ሳይ ክስ የመሰረቱት በመካከላቸዉ በተፈጸመ የተሽከርካሪ ሽያጭ ዉል መሰረት አመልካች በሽያጭ ያስተላለፈላቸዉ ተሽከርካሪ የባትሪ ጉድለት ስላለበት አገልግሎት መስጠት ስላልቻለ አመልካች በዉሉ መሰረት ተሽከርካሪዉ ያለበትን ጉድለት እንዲያስተካክል እንዲወሰንላቸዉ አሊያም አመልካች የዉሉን ግዴታ በአግባቡ ስላልተወጣ ዉሉ ተሰርዞ አመልካች የተቀበለዉን የተሽከርካሪዉን ዋጋ እንዲመልስና በተሽከርካሪዉ የትራንስፖርት አገልግሎት ቢሰጡ ኖሮ ያገኙ የነበረዉን ነገር ግን ተሽከርካሪዉ ባለበት ጉድለት ምክንያት መገልገል ባለመቻላቸዉ ያጡትን እንዲከፍሏቸዉ እንዲወሰን ዳኝነት በመጠየቅ ነዉ።አመልካች ደግሞ በሽያጭ ዉሉ መሰረት ተጠሪ ጉድለት የሌለበትን ተሽከርካሪ እንደተረከቡ፤ጉድለቱ በአጠቃቀም ምክንያት የተከሰተ እንደሆነ፤ተጠሪ በዉሉ መሰረት በሶስት ወር ዉስጥ ማሳወቅ ሲገባቸዉ ከ3 ዓመት በላይ ሳያሳዉቁ እንዳቆዩ በመግለጽ ክሱ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2298/1 መሰረት በይርጋ እንደሚታገድ አሊያም ጉድለቱ መሰረታዊ ስላልሆነና የተከሰተዉም በተጠሪ ምክንያት በመሆኑ ክሱ ዉድቅ ሲሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል።አመልካች ለተጠሪ በቀን 15/07/2007ዓ/ም በተደረገ የሽየጭ ዉል የሸጠዉ ተሽከርካሪ ኪነቲክ ዊንግ ባጃጅ (kinetic wing) የሚባል ተሽከርካሪ እንደሆነ፤ የተሽከርካሪዉን ዋጋ ብር 69,999.99 ተጠሪ ለአመልካች መክፈላቸዉን፤ተጠሪ ተሽከርካሪዉን በባለሙያ አስፈትሸዉ መረከባቸዉን ፤ ጉድለቱን ተጠሪ ለአመልካች ያሳወቁት በቀን 15/06/2009ዓ/ም እንዲሁም ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ክሱን የመሰረቱት በቀን 07/03/2012ዓ/ም መሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ከግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃዎች ያረጋገጡት ፍሬ ነገሮች ናቸዉ።የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክሱ በይርጋ አልታገደም በሚል የአመልካችን መቃወሚያ ዉድቅ ያደረገዉ ተጠሪ ክስ ያልመሰረቱት አጎታቸዉ የአመልካች የቦርድ አባል ስለሆኑ ባላቸዉ ዝምድና አጎታቸዉን በመፍራትና በማክበር እንደሆነ በመግለጽ ያቀረቡትን ክርክር በመቀበል ነዉ።

አመልካች የይርጋ መቃወሚያ ያቀረበዉ የተጠሪ ክስ የማቅረብ መብት በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 2298 መሠረት በአንድ ዓመት ይርጋ ቀሪ ሆኗል በሚል ሲሆን በዚህ ችሎት ባቀረበዉ አቤቱታም ይህንኑ በማጠናከር ተከራክሯል። በእርግጥ ዕቃዉ (በተያዘዉ ጉዳይ ተሽከርካሪዉ) በዉሉ ላይ በተመለከተዉ አግባብ ተሟልቶ አልቀረበም ወይም ጉድለት አለበት የሚል ገዥ ዕቃዉ ጉድለት ያለበት መሆኑን ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ዉስጥ የዋቢነት ክስ በሻጭ ላይ ማቅረብ እንደሚችል እና ከዚህ ጊዜ በኋላ የሚቀርበዉ ክስ ተቀባይነት እንደሌለዉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2298 ላይ ተደንግጓል። ከዚህ በግልጽ መገንዘብ የሚቻለዉ ይህ የአንድ ዓመቱ የይርጋ ድንጋጌ የዋቢነት ክስን የሚመለከት መሆኑን ነዉ።የዚህ ድንጋጌ አፈጻጸም ይሄዉ ስለመሆኑ ይህ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 206816(ያልታተመ) ላይ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል። ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ለጠየቁት ዳኝነት መሰረት ያደረጉት አመልካች የባትሪ ጉድለት ያለበትን ተሽከርካሪ ስለአስረከበኝ እንደዉሉ ስላልፈጸመ በዉሉ መሰረት አስተካክሎ እንዲፈጽም ይወሰንልኝ በማለት የጠየቀዉ ዳኝነት ጥያቄ ተሽከርካሪዉ ያለበትን ጉድለት ያስተካክልልኝ የሚል ዳኝነት ጥያቄ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2298 ስር

*ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

በተደነገገዉ መሰረት በአንድ አመት ዉስጥ ክስ በማቅረብ መጠየቅ ያለባቸዉ ዳኝነት ጥያቄ ነዉ፡፡ የተሸከርካሪ ሽያጭ ዉል የተደረገዉ በቀን 15/07/2007ዓ/ም ሆኖ ክሱን ያቀረቡት ደግሞ በቀን 07/03/2012ዓ/ም በመሆኑ ይህንን ዳኝነት ጥያቄያቸዉን በተመለከተ ክስ የማቅረብ መብታቸዉ በይርጋ ቀሪ ሆኗል፡፡

በሌላ በኩል ተጠሪ የክስ ምክንያታቸዉ አመልካች የባትሪ ጉድለት ያለበትን ተሸከርካሪ በሽያጭ አስተላልፎልኛል የሚል ቢሆንም በተጨማሪነት የጠየቁት ዳኝነት ጥያቄዎች በዉሉ ላይ ከተመለከተዉ ዉጭ ጉድለት ያለበትን ተሸከርካሪ ስላስረከበኝ በተሸከርካሪዉ ሰርቼ ማግኘት ያለብኝን ገቢ አጥቻለሁ በማለት አጣሁኝ ያሉትን ገቢ ስማስከፈል እና ዉሉ እንዲሰረዝ ነዉ፡፡ በዚህ መልኩ በተጨማሪነት የጠየቁት ዳኝነት እንደዉሉ እንደዉሉ ባለመፈጸሙ ምክንያት ለደረሰ ጉዳት ካሳ እንዲከፈላቸዉ እና ዉሉ እንዲሰረዝ (actions for cancellation of a contract and damage) ዳኝነት ጠይቀዉበት ያቀረቡት ክስ ነዉ፡፡ እነዚህን ዳኝነት ጥያቄዎች በሚመለከተዉ የክስ ክፍል ላይ ተፈጻሚነት ያለዉ የይርጋ ጊዜ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1845 ስር የተደነገገዉ የ10 ዓመት የይርጋ ጊዜ እንጂ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2298 ስር ተደነገገዉ አይደለም፡፡ከዚህ አኳያ ሲታይ በግራ ቀኙ መካከል ለክሱ መነሻ የሆነዉ የተሸከርካሪ ሽያጭ ዉል የተደረገዉ በቀን 15/07/2007ዓ/ም ክሱ የቀረበዉ ደግሞ በቀን 07/03/2012ዓ/ም በመሆኑ 10 ዓመት ሳያልፍ የቀረበ ክስ ስለሆነ ክስ ያማቅረብ መብታቸዉ በይርጋ ቀሪ አልሆነም፡፡

በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን ከላይ ከተመለከተዉ አንጻር ማየት ሲገባዉ አመልካች የራሱ የሆነ ሕጋዊ ሰዉነት ያለዉ የንግድ ድርጅት ሆኖ እያለ፣ የዉል ግዴታዉን አልተወጣም ተብሎ የተከሰሰዉም አመልካች ድርጅት እንጂ የድርጅቱ የቦርድ ወይም የቦርድ አባል ባልሆነበት ተጠሪ ክሱን ሳያቀርቡ የቆየት የአመልካች ድርጅት የቦርድ አባል የሆኑት አጎታቸዉ ስለሆኑ ካላቸዉ ዝምድና አጎታቸዉን በመፍራትና በማክበር እንደሆነ ገልጸዉ ያቀረቡትን መከራከሪያ መሰረት በማድረግ ክሱ በይርጋ ቀሪ አልሆነም የሚል ድምዳሜ ላይ መድረሱ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1853/1 ስር የተደነገገዉን መንፈስና ዓላማ የተከተለ ካለመሆኑም በተጨማሪ የተሸከርካሪዉ ጉድለት ይስተካከልልኝ በማለት ተጠሪ ለጠየቁት ዳኝነት ተፈጻሚነት ያለዉን በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2298 ስር የተደነገገዉን የይርጋ ጊዜ ያልተከተለ በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ ስህተት ነዉ ብለናል፡፡ሆኖም ሌሎች ዳኝነት ጥያቄዎችን በተመለከተ ክሱ በይርጋ ቀሪ አልሆነም የሚለዉ መደምደሚያ ተገቢ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት የይርጋ መቃወሚያዉን ዉድቅ በማድረግ የሰጠዉን ዉሳኔ ከዉጤት አንጻር በማየት ተቀብለናል፡፡

በሌላ በኩል የተሸከርካሪ ሽያጭ ዉል ፈርሶ ግራ ቀኙ ወደነበሩበት እንዲመለሱ በመወሰኑ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን በተመለከተ የተያዘዉን ጭብጥ እንደመረመርነዉ ተጠሪ ተሸከርካሪዉ አለበት ያሉት ጉድለት የባትሪ እንደሆነ በግራ ቀኙ የታመነ ጉዳይ ነዉ፡፡እንዲሁም ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን ያየዉ ፍርድ ቤት ማስረጃዎችን መርምሮና መዝኖ ተጠሪ ተሸከርካሪዉን ገዝተዉ ከመረከባቸዉ በፊት በራሳቸዉ ባለሙያ ተሸከርካሪዉን አስፈትሸዉ ጉድለት እንደሌለበት አረጋገጠዉ ገዝተዋል፣ ጉድለት የሌለበትን ተሸከርካሪ

መረከባቸዉ ተረጋግጧል፤ በዉሉ በተመለከተዉ መሰረት በባትሪዉ ላይ ጉድለት ካለበትም በ3 ወር ጊዜ ዉስጥ ለአመልካች ማሳወቅ ሲገባቸዉ ለ3 ዓመታት በግቢዉ ዉስጥ አቁመዉ በማቆየታቸዉ ጉድለቱ የተከሰተዉ በተጠሪ ቸልተኝነት ነዉ የሚል የፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ ደርሰዋል፡፡የስር ፍርድ ቤት በዚህ መልኩ የሰጠዉን ዉሳኔ ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት የሻረዉ አመልካች ተሽከርካሪዉን ያስረከበዉ ከእነ ጉድለቱ መሆኑን እና ተጠሪ ለአመልካች የተሽከርካሪዉን ጉድለት ከ3 ዓመት በኋላ ከማሳወቁ ጋር ተያይዞ በጊዜ ቆይታ ብዛት ይህ ጉድለት በተሽከርካሪዉ ላይ እንዳልደረሰ ተጠሪ በማስረጃ ያስረዱት ነገር በሌለበት ነዉ፡፡ በአንጻሩ ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት "እንዲህ አይነት ተሽከርካሪ በሐረር ከተማ ዉስጥ ሰሌዳ አዉጥቶ የታክሲ ትራንስፖርት አገልግሎት እየሰጠ ስላልሆነ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2289 መሰረት ተሽከርካሪዉ ጉድለት እንዳለበት ያሳያል፤ ተጠሪ ተሽከርካሪዉ ለታክሲ አገልግሎት እንደማይዉል ቢያዉቁ ኖሮ ግዥ የማይፈጽሙ መሆኑን ፍርድ ቤቱ ተረድቷል፡፡" ሲል የደረሰበት ድምዳሜ በተጨባጭ ማስረጃ ላይ ሳይሆን በግምት ላይ የተመሰረተ እንደሆነ ያሳያል፡፡ይህ ተሽከርካሪ በሐረር ከተማ ዉስጥ የታክሲ አገልግሎት እየሰጠ እንዳልሆነ ተረጋግጦ ቢሆን እንኳን እንዲህ አይነት ተሽከርካሪዎች በከተማዉ የታክስ አገልግሎት መስጠት ያልቻሉት ካለባቸዉ የአሰራር ጉድለት ችግር ምክንያት እንደሆነ የሚያሳይ ማስረጃ የሚሆን የባለሙያ ማረጋገጫ ቀርቦ ባልተረጋገጠበት አመልካች ለተጠሪ የሸጠዉ ተሽከርካሪ ከመነሻዉም ለትራንስፖርት አገልግሎት እንዳይዉል የሚያደርግ ጉድለት የነበረበት ነዉ ብሎ ለመደምደም የሚያስችል የሕግም ሆነ የፍሬ ነገር መሰረት ያለዉ ድምዳሜ ሊሆን አይችልም፡፡

ተጠሪ ተሽከርካሪዉ ጉድለት አለበት የሚሉ ከሆነ ለጉድለቱ አመልካች ዋቢ እንዲሆንላቸዉ ለመጠየቅ መብት እያላቸዉ ይህንን መብታቸዉን በዉሉ በተመለከተዉ 3 ወር ጊዜ ዉስጥ አሲያም በሕጉ አንቀጽ 2298 ላይ በተመለከተዉ የአንድ ዓመት ጊዜ ዉስጥ ለፍርድ ቤት ክስ አቅርበዉ ጉድለቱ እንዲስተካከል በመጠየቅ መብታቸዉን አለማስከበራቸዉ መብታቸዉን እንደተዉ ይቆጠራል፡፡ከዚህ ጋር ተመሳሳይ በሆነ ጉዳይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 55229(ቅጽ 12 ላይ እንደታተመዉ) ላይ የተሰጠዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉምም ይህንኑ የሚያስገንዘብ ነዉ፡፡ እንዲሁም በተሽርካሪዉ ባትሪ ላይ አለ የተባለዉ ጉድለት ተሽከርካሪዉን በይዞታቸዉ ስር አድርገዉ ከ3 ዓመት በላይ አቁመዉ በማቆየታቸዉ በራሳቸዉ ቸልተኝነት ምክንያት የደረሰ ጉዳት እንደሆነ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያረጋገጠዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ተሽከርካሪዉን በራሳቸዉ ባለሙያ አስፈትሸዉ ችግር የሌለበትን እንደተረከቡ የስር ፍርድ ቤት በማስረጃ ከማረጋገጡም በተጨማሪ ተሽከርካሪዉ አለበት የተባለዉ የባትሪ ችግር መሰረታዊ ነዉ እንኳን ቢባል ይህ ጉድለት ያለበትን ተሽከርካሪ አመልካች አጭበርብሮ ወይም በተንኮል ጉድለቱን ደብቆ ያስረከባቸዉ ስለመሆኑ ያሳስረዱ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2297 መሰረት ዉሉን ሊያስፈርስ የሚችል ምክንያት አይደለም፡፡

ስለሆነም ይግባኝ ሰሚዉ የሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በግራ ቀኝ መካከል የተደረገዉን ዉል ሊያስፈርስ የሚችል በሕግ ተቀባይነት ያለዉ ምክንያት ሳይኖር የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፍሬ ነገርን በተገቢዉ ማስረጃ አረጋግጦ የሰጠዉንና የሕግ ድጋፍ ያለዉን ዉሳኔ የሕግ ድጋፍ በሌለዉ ምክንያት ላይ ተመስርቶ በግራ ቀኙ

መካከል የተደረገዉ የተሽከርካሪ ሽያጭ ዉል እንዲፈርስ የሰጠዉ ዉሳኔ ሲታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10(1/ሐ) መሰረት የሚከተለዉን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 05072 ላይ በቀን 13/11/2013 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 00230 ላይ በቀን 07/03/2014ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. የሐረሪ ክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 17126 በቀን 13/05/2012 ዓ/ም የሠጠዉ ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ፀንቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

1. የውሳኔው ግልባጭ ለግራ ቀኙ ይሰጣቸዉ፤ለሥር ፍርድ ቤቶችም ይተላለፍ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጥ

*ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*